# ክፍል ሦስት
# አማናዊት ቤተክርስቲያን
## ምዕራፍ አንድ
## ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ የነበረው የዓለም ሁኔታ

ክርስቶስ ሲወለድ ምድረ ፍልስጥኤም እንደሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ፣ የሰሜን አፍሪካና የታናሽ እስያ አገሮች በሮም ቅኝ ግዛት ሥር ነበረች:: በውስጥዋ የነበሩ ሕዝቦችም የተከፋፈለ የሃይማኖትና የፖለቲካ ቡድን ነበራቸው:: ከእነዚህም የሃይማኖት ቡድኖች ዋና ዋናዎቹ ኤሴዎች፣ ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያን ነበሩ::

### ሀ. ፈሪሳውያን

ፈሪሳዊ «ፓራሽ» ከሚለው የእብራይስጥ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም የተለየ ማለት ነው:: እነዚህ ወገኖች አፍአዊ ትዕዛዛትን ብቻ በመጠበቅ የሕግ ፈጻሚ መስለው የሚታዩ እንደነርሱ እርምጃ የማይሄደውን የሚወቅሱ፣ የሚከሱ ነበሩ:: ፈሪሳውያን ምንም የቅኝ አገዛዝ ቀንበር መላልሶ ቢያደቃቸውም ባህልና ልምዳችን አይነካም የሚሉ ነበሩ::

በሃይማኖትም የሙሴ የሕግ መጻሕፍትንና የነቢያትን የትንቢት መጽሐፍ የምንቀበል እኛ ብቻ ነን፣ ፈጻሚዎቹ እኛ ነን ይላሉ:: ከአይሁድ ዘር ውጭ የሆነ ከማንኛውም ጎሣና ዘር ጋር በባህልና በሥልጣኔ መቀራረብን እንደመርከስ ሕግን እንደመተላለፍ ይቆጥሩ ነበር:: የመሲህን መምጣት ነቅተው ተግተው ይጠባበቁ ነበር:: ከትንሣኤ ሙታን በኋላ ሥጋዊ ኑሮ አለ ብለው ቢያምኑም ትንሣኤ ሙታንን ያምናሉ:: መጠነኛ እውቀትና ብዙ ሀብትም የሌላቸው ሰዎች ናቸው:: የመሲህን መምጣት ይጠባበቁ የነበሩት የጦር ኃይል አቋቁሞ የጦር አበጋዝ ሆኖ ከሮማውያን ቅኝ አገዛዝ ያወጣናል ብለው ነበር::

### ለ. ሰዱቃውያን

እነዚህ ወገኖች የፈሪሳውያን ተቃራኒ ናቸው:: ቡድኑም የሀብታምና የካህናት ቡድን ነው:: ስለ ሥነ-ሥርዓትና ስለ ሃይማኖት ግድ የለሾች ነበሩ:: ከቅኝ ገዥዎችም ጋር ተስማምተው በእነርሱ ሥልጣን ለመጠቀም ብቻ የሚፈልጉ ነበሩ:: ከሃይማኖት መጻሕፍትም የሙሴን ሕግ ብቻ ይጠቀሙ ነበር:: በራሳቸው አስተያየትም ይተረጉሙት ስለነበር በትንሣኤ ሙታን፣ በመናፍስትና በሚመጣው ዓለም ሰው እንደ ሥራው ዋጋውን ይቀበላል የሚለውን አያምኑትም ነበር:: ማቴ. 22÷23-33፣ ዘዳ. 25÷5-10፣ የሐዋ. ሥራ 23÷8፣ ማር. 12÷19፣ ሉቃስ 20÷28::

ሐ. ኤሴዎች /ኤሲያውያን/

እነዚህ ወገኖች ደግሞ የመናንያን ማኅበር ነበሩ:: ከፈሪሳውያን ጋር በአስተሳሰብ ተጣልተው ከፈሪሳውያን የተገነጠሉ ነበሩ:: ኩምራን በምትባለው ቦታ በሙት ባህር /ጨው ባህር/ የሎጥ ባህር አካባቢ ገዳም ገድመው ክርስቶስ ሲመጣ በተአምራት ከጠላቶቻችን እጅ ነፃ ያወጣናል ባዮች ነበሩ:: በገዳማቸውም በጾም በጸሎት በትምህርት የሚኖሩ ነበሩ::

## የመሲህ መምጣት ተስፋ

ዓለም በዚህ በተመሰቃቀለ ማኀበራዊ ኑሮ ሲኖር ከቶ ደስ ብሎት በኑሮው አምኖበት የሚኖር አልነበረም:: ብዙ ነቢያት ስለ መሲህ መምጣት አስፋፍተው ተናግረው ነበር:: ይህ ትንቢት የተጠቀሰው በእስራኤል ብቻ በመሆኑ የእስራኤል ተስፋ አሁንም መሲህ መጥቶ ከአለባቸው ችግር እንዲያድናቸው ከሮማውያን የባርነት ግዛት ነፃ እንዲያወጣቸው ይጠብቁ ነበር::

አረማውያን ደግሞ የሰውን ጨካኝነት የክፋቱን ብዛት ከቀን ወደ ቀን እየባሰ መሄዱን አይተው ከአምላክ አንድ ምሕረት ካልተሳከ በቀር በሰው ኃይል ድኅነት ሊደረግ የማይችል እንደሆነ ያውቁ ነበር::

የእስራኤል ተስፋ ሙሉ ቢሆንም መሲህ እንደሚመጣ ተስፋ ቢያደርጉም የመሲሁን መምጣት ይጠባበቁ የነበረው አንድ መሲህ ተነስቶ አገሯን ከባዕድ አገዛዝ ነፃ አውጥቶ የዳዊት የሰሎሞንን መንግሥት መልሶ በሰላም የሚያስተዳድር አድርገው ነበር እንጂ አምላክ ወልደ አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ዓለምን እንደሚያድን አያምኑም ነበር::

የሰው ወገን የሆነ ሁሉ ደክሞት መኖር ሰልችቶት ሁሉም በየበኩሉ ይቆዝም ነበረ:: ሀብታሙ በሀብቱ ደስታን ለመሸመት አልሆንለት ብሉ፣ መበለታት ወይት ወደታችሁ የሚላቸው አልነበረም:: በሽተኞችና ረሀብተኞች ጥርኝ ጥሬ፣ ኩባያ ውሃ የሚላቸው አጥተው በረሀብ ይተላለቁ ነበር::

ዓለም በዚህ መልክ በሚገኝበት በጭንቅ ጊዜ የቤተክርስቲያን መሠረት፣ የአሕዛብ ብርሃን፣ የእስራኤል ዘነፍስ ክብር፣ የዓለሙ መድኃኒት የሆነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም /ወላዲተ አምላክ/ ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ በሮም ቅኝ ግዛት ሥር በነበረች በፍልስጥኤም ልዩ ስሟ ቤተልሔም በምትባል ክፍል በሥጋ ተገለጠ ማለት ሰው ሆኖ ተወለደ::

## የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የዘመነ ሥጋዌ ጉዞ ብሥራት

**ብስራት፡-**

እግዚአብሔር መንፈሱን የሚያሳርፍበት የበቃ ሰው ባልነበረበት ጊዜ በነፍስም በሥጋም ንጽሕት የሆነች የእግዚአብሔርን ቃል በማኅፀኗ ለመሸከም የበቃች በናዝሬት ከተማ የምትኖር አንዲት ድንግል ነበረች፡፡ የዚህችም ድንግል ስሟ ማርያም ነበር፡፡ ሉቃስ 1÷27፡፡ እግዚአብሔር የዓለሙ ድኅነት ፈቃዱ ስለሆነ ለዚህ ዓለም ድኅነት ምክንያት ይህችን ድንግል መረጠ፡፡ ስለዚህም በፊቱ የሚቆመውን ባለሟሉን መልአክ ቅዱስ ገብርኤልን የምሥራች ይናገር ዘንድ ወደ እርሷ ላከ፡፡ መልአኩም ወደዚያች ድንግል በደረሰ ጊዜ «ደስ ይበልሽ ጸጋን የሞላብሽ ሆይ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት» ሉቃስ 1÷28፡፡ ቅድስት ማርያምም እውነተኛ ስለነበረች በውዳሴ ከንቱ አልተጠለፈችም፡፡ ስለዚህ ወዲያውኑ አልተ ቀበለችውም ነበርና «ወንድ የማላውቅ ስሆን ይህ እንደምን ይሆናል?» ብላ ጠየቀችው፡፡ መልአኩም የተላከበት ነገር ነውና በብዙ አስረጂ አስረዳትና ማሠሪያውን «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም» አላት፡፡ ቅድስት ማርያምም «ብእርግጥ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና እነሆ የእግዚአብሔር ገረዱ አለሁኝ እንደቃልህ ይሁንልኝ» አለችው፡፡ ሉቃስ 1÷37፡፡ በዚህ ጊዜ አካላዊ ቃል በማኅፀኗ ተቀረፀ፡፡

### የኤልሳቤጥ ምስክርነት፡-

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የመልአኩን ብሥራት እንደሰማች ወዲያውኑ አክስቷ ኤልሳቤጥ ወደምትገኝበት ወደ ይሁዳ ሄደች፡፡ ሉቃስ 1÷39፡፡

ከኤልሳቤጥም ዘንድ ደርሳ ሰላምታ እንደተሰጣጡ በኤልሳቤጥ ላይ መንፈስ ቅዱስ ሞላባትና የቅዱስ ገብርኤልን ቃል በመድገም «አንቺ ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ የማህፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው» ብላ ብፅዕናዋን፣ ቅድስናዋን፣ የጌታም እናት መሆኗን ተናገረች፡፡ ሉቃስ 1÷41-45፡፡ ቅድስት ድንግል ማርያምም ከሰማያውያን መላእክት የቅዱስ ገብርኤልን፣ ከምድራውያን ከኤልሳቤጥ ከሁለት ወገን ምስክር ስላገኘች ስባሰውለታው አምላክ ምስጋና አቀረበች፡፡ ሉቃስ 1÷46-55፡፡

### የክርስቶስ ልደት፡-

በሮማ አውግስጦስ ቄሣር በነገሠ፣ በሶርያም ቄሬኔዎስ ገዥ በነበ ረበት ጊዜ በኢየሩሳሌምና በአውራጃዋም ሄሮድስ በነገሠ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ እንዲቆጠር /እንዲጻፍ/ ቄሣር በሰጠው አዋጅ የእመቤታችንና የቅዱስ ዮሴፍ አገር ይሁዳ /ቤተልሔም/ ነበርና በአዋጁ መሠረት ሊቆጠሩ እንደመጡ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሐም ተወለደ:: ሉቃስ 2÷1:: ለቆጠራው የመጣው ሰው በዝቶ ቦታውን ይዞት ስለነበር እመቤታችንና ዮሴፍ ማደሪያ አጥተው በአንድ በረት እንደሠፈሩ የጌታችን ልደት በዚያው በበረት ሆነ:: ሆኖም አምላክ ነውና እንደ አምላክነቱ ከእንስሳት ወገን ላህምና አህያ እስትንፋሳቸውን ገበሩለት:: ሉቃስ 2÷8-20:: የሰማይ ሠራዊት ደግሞ «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ» እያሉ በምስጋና ተቀበሉት:: ተቋርጦ የነበረው ሥራቸው ተጀምሯልና:: እረኞችም ከብርሃኑ ብዛት ከሰማይ ሠራዊትም ምስጋና ድምጽ የተነሳ ይደነቁ ምስጋናም ያቀርቡ ነበር:: ሉቃስ 2÷8-20::

እንዲሁም የጥበብ ሰዎች ከምሥራቅ ረጅም ጉዞዋቸው መጥተው ሰገዱለት፣ ወርቅ ለመንግሥቱ፣ ዕጣን ለክህነቱ፣ ከርቤም ለሞቱ ምሳሌነት አድረገው ገበሩለት:: ማቴ.2÷1-12:: ቅድስት ድንግል ማርያም ግን የሆነውን ሁሉ ታስተውል በልብዋም ትጠብቅ ነበር:: ታላላቅ ተአምራት ሲያደርግ አይታለችና:: ይኸውም በኀቱም ድንግልና ፀንሳ በኀቱም ድንግልና መውለድዋ፣ የሰማይ ሠራዊት መጥተው ምስጋና ማቅረብ፣ ይህ ሁሉ ተጠቃሎ ማየት ታላቅነት የሚገልጥ ነው:: ሉቃስ 2÷19::

## ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግን እየፈጸመ ማደጉን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስምንተኛው ቀን ተገረዘ:: ሉቃስ 2÷21:: በአርባ ቀንም ወደ ቤተ መቅደስ ተወሰደ:: እዚያም ስምዖን አቀፈው ሐናም አየችው:: ሉቃስ 2÷21-38::

## የጌታችንና የመድኃኒታችን ስደት ወደ ግብፅ

የምሥራቅ ሰዎች ሲመጡ የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው የተወለደው እያሉ የክርስቶስን ንጉሥነት እየመሰከሩ ስለመጡ ማቴ. 2÷1-4 ሔሮድስ ንጉሥ ከሆነማ «ንጉሥ ሳይገድል አይነግሥም በኔ ላይ የሚሰለጥን እንዴት ያለ ንጉሥ ተወለደብኝ» በማለት ጌታን ይገድል ዘንድ አሰበ:: ስለዚህም ወደ ግብጽ እንዲሰደዱ ምክሩን የሚለግስ መልአክ ከእግዚአብሔር ታዘዘ:: እርሱም በሌሊት በራዕይ ለዮሴፍ ታየው:: ተናገረውም እንዲህ ሲል «ተነሳና እናቱንና ሕፃኑን ይዘህ በሌሊት ወደ ግብፅ ሽሽ፣ ሄሮድስም ህፃኑን ይገድለው ዘንድ አሰውና» አለው:: ዮሴፍ ቅድስት ድንግል ማርያምንና ሕፃኑን ይዞ በሌሊት ወደ ግብፅ ተሰደደ:: ማቴ. 2÷13-15፣ ሆሴዕ 11÷1:: ከዚያም ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወር 3 ዓመት ከመንፈቅ ቆየ፣ ሔሮድስ እንደሞተ ያው መልአክ ለዮሴፍ ከግብፅ እንዲመለስ አመለከተውና ወደ ናዝሬት ሄደ ጌታም በዚያ አደገ:: ማቴ. 2÷19-23 ::

## የክርስቶስ የህፃንነቱ ጊዜ

ከግብፅ ስደት ከተመለሱ በኋላ ጌታችን ቤተሰቦቹም መኖሪያቸው ናዝሬት ነበር:: ማቴ. 2÷23:: ናዝሬትም የገሊላ አውራጃ ከተማ ነበረች:: እንደሌሎች አወራጃ ከተሞችዋ ዝነኛ አልነበረችም:: ስለዚህ የዕለት ምግቡን ያገኝ የነበረው እንጨት እየጠረበ ለቤት አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎችን እየሠራ በመሸጥ ነበር:: ጌታችን ከዮሴፍ ጋር በመኖሩ ይህን ሥራ እንደሠራ ይገመታል:: ሆኖም በዚያው በናዝሬት አደገ፤ ጥበብን እየተሞላ በመንፈስ እየጠነከረ ይሄድ ነበር:: ምክንያቱም ጌታችን ግዕዘ ሕፃናትን አላፋለሰም:: እንደማንኛውም ህፃን ቀስ በቀስ እያለ ነው ያደገው::

በ12 ዓመቱ ከዘመዶቹ ጋር ለበዓል ኢየሩሳሌም ሄዶ እንደነበር እናገኛለን:: ሉቃስ 2÷41-51:: ምክንያቱም እመቤታችንና ዮሴፍ በዓመቱ እንደ አይሁድ ሥርዓት /ልማድ ለበዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ነበርና:: ዘፀ.23÷14-17:: ኦሪት በዓመት ሦስት ጊዜ በእናንተ ዘንድ ያለ ወንድ ሁሉ በጌታ በእግዚአብሔር ፊት ይታይ ትል ስለነበር::

በዚያም በኢየሩሳሌም በሊቃውንቱ መካከል ሆኖ ሲጠይቃቸውም ሲሰማቸውም ተገኝቷል:: ሉቃስ 2÷46-48:: ይህም ማለት የዕብራውያንን ሥርዓት በመከተል የዕብራውያንን ትምህርት እየተማረ እንዳደገ ያስረዳል:: አባ ሕርያቆስ ይህን ሲያስረዳ «የዕብራውያንን ሕግ ተማረ» ብሏል:: ስለዚህ የዕብራውያን ሕግ የፀና ሆነ:: ጌታችንም በዚህ በናዝሬት እየኖረ በጥበብም፣ በቁመትም አደገ:: በእግዚአብሔርና በሰው ፊትም ሞገስን አገኘ፣ ቤተ ዘመዶቹን ይታዘዝ ያገለግልም ነበር:: ሉቃስ 2÷25:: ከሠላሳ ዓመት ዕ ድሜው በኋላ በመምህርነት እስከ ተገለጠበት ድረስ ተራ ሰው መስሎ በዚያው በናዝሬት ኖረ:: በዚህም ዘመን ሰው የሚሠራውን ሁሉ ከኃጢአት በቀር ሠራ:: አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ከኃጢአት ብቻ በቀር የሰውን ሕግ ሁሉ ፈፀመ እንዳለ::

## የክርስቶስ ጥምቀት

ጌታችን የሕፃንነቱን ዘመን ፈጽሞ ልክ ሠላሳ ዓመት ሲሞላው የይፋ ሥራውን ለመሥራት ከናዝሬት ወጣ ወደ ይሁዳም ሄደ:: የይፋ ሥራውንም በጥምቀት ጀመረ:: ዮሐንስ በዮርዳኖስ ምድረ በዳ «ንስሐ ግቡ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና» እያለ እያስተማረ ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ የንስሐ ጥምቀት እያጠመቀ የክርስቶስን መንገድ እየጠ ረገ እያዘጋጀም መጣ:: ክርስቶስ ከዮሐንስ ጋር በተገናኘ ጊዜ እንዲያጠምቀው ጠየቀው፤ ዮሐንስ ግን «እኔ በአንተ ልጠመቅ እወዳለሁ

እንጂ አንተ ከኔ እንዴት ትጠመቃለህ» ሲል አይሆንም አለው:: ጌታችን ግን «አንድ ጊዜ ተው፤ የተነገረው ሁሉ እውነት ነው:: እርሱንም እንፈጽም ዘንድ ይገባናልና» አለው:: በዚህ ጊዜ ተወውና አብረው ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሄዱና ዮሐንስ አጠመቀው፣ ጌታችንም ተጠመቀ:: ማቴ.3÷13-17፣ማር.1÷9-11፣ሉቃስ 3÷21-23፣ ዮሐ.1÷32-34፣ ኢሳ.40÷3::

ጌታችንም ተጠምቆ ከውኃ እንደወጣ ከሰማይ ቃል መጣ:: «ይህ ነው የምወደው ልጄ» የሚለውን፣ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል በራሱ ላይ ሲያርፍ ታየ:: በዚህን ጊዜ ሦስትነቱ ተገለጠ፤ ማለትም ወልድ ሲጠመቅ፣ አብ በሰማይ ሆኖ ድምጽን ሲያሰማ፣ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ ሲያርፍበት::

## የክርስቶስ ጾም

ክርስቶስ እንደተጠመቀ ወዲያውኑ በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ወደ ምድረ በዳ ሄደ:: በዚያም 40 መዓልት 40 ሌሊት ጾመ:: ከዚህ በኋላ ተራበ:: ፈታኙ ሰይጣንም እንደተራብ ባየ ጊዜ አዳምን በመብል እንዳሳትኩት ክርስቶስንም በምግብ አስታለሁ ብሎ «የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እነዚህን ድንጋዮች ሕብስት እንዲሆኑ እዘዝ» አለው:: ክርስቶስ ግን ለፈቃዱ አልታዘዘለትም፤ እንዲያውም «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ከእግዚአብሔር በሚወጣው ቃልም ነው እንጂ» ሲል መለሰለት ማቴ. 4÷4፣ ዘዳ8÷3:: ሁለተኛም ወደ ቤተመቅደስ ወስዶ ከተቀዋቡ ላይ አውጥቶ «ከዚህ ዘለህ ውረድ ስለ አንተ መላእክትን ያዛቸዋል፤በጎዳናህ ሁሉ እንዲጠብቁህ፣ እግርህም በእንቅፋት እንዳትሰናከል የሚል ጽሑፍ አለና» አለው:: ጌታችንም መልሶ «ፈጣሪህ እግዚአብሔ ርን አትፈታተን» የሚለውን መለሰለት:: ማንኛውም የማይገባውን እየሠሩ እግዚአብሔ ር ይሆን ያደርግብኛል የሚለው ሁሉ የማይረባ መሆኑን ጠቅሶ አስረዳው:: ማቴ.4÷5-7፣ መዝ. 90÷11-12:: ሦስተኛ እንደገና ከረጅም ተራራ አወጣውና የዓለምን መንግሥታት ክብራቸውን አሳይቶ «ለኔ ብትታዘዝ ብትሰግድልኝ ብታመልከኝ ይህን ሁሉ ለአንተ እሰጥሀለሁ» ብሎ በሚያስጎመጅ አገላለጥ ገለጠለት:: ጌታችን ግን ከክብር ዙፋን የወረደው ወደ እዚህ ዓለም የመጣው ለሰው ድኅነት እንጂ ለራሱ ክብር አይደለምና «ሰይጣን ባለጋራዬ ወግድ ከኋላዬ» ሲል ለአምላክ የአምልኮ ስግደት መስጠ ገድና አምላክን ብቻ ማምለክ እንዲገባ አስረድቶ ለጊዜው ከሱ ራቀ:: መላእክቱም ሊያገለግሉት መጡ:: ማቴ. 4÷11::

## የሐዋርያት መጠራት

ክርስቶስ ጾሙን ከፈጸመ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን መሰብሰብ ጀመ ረ፣ ገሚሱ በአሣ አጥማጅነት ሲሠሩ/ ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ቅዱስ እንድርያስ፣ ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዲዮስ፣ ወንድሙ ቅዱስ ዮሐንስ ማቴ. 4÷8-22፣

ማር. 1÷20፣ ሉቃስ 5÷2-11/ ሌላውም እንዲሁ ከመቅረጫው ቅዱስ ማቴዎስ ወልደ እልፍዮስ ማቴ.9÷9፣ ማር.2÷14፣ ሉቃስ 5÷27:: ሌላውም እንዲሁ በመንገድ እያለ የክርስቶስ ጥሪ የደረሰውና ለመከተል ፈቃደኛ ሆነው እየተ ሰናበቱ ተከተሉት:: ዮሐ. 1÷34-53:: ይህ ሁሉ የተፈጸመው ከጾሙ በኋላ ባሉት ቀናት ባደረገው ትምህርት ነው:: ማር.3÷13-19፣ ሉቃስ 6÷14-16::

## ቅዱሳን ሐዋርያት

ፈጣሬ ፍጥረታት መጋቤ ዓለማ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ በተለየ አካሉ በቃልነት ከዊኑ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ተወልዶ በ30 ዘመኑ ተጠምቆ አርባ ቀን አርባ ሌሊት ከጾመ ከጸለየ በኋላ ወንጌለ መንግሥትን ድኅነተ ዓለምን ተምረው አውቀው የሚያስተምሩ የሚያሳውቁ ሰዎችን መረጠ:: እነዚህም የተመረጡት ደቀመዛሙርት (ሐዋርያት ) ይባሉ::

ሐዋርያ ማለት ሂያጅ፣ ገስጋሽ፣ ምጥው፣ ፍንው፣ ማለት ነው የተማሩትን ዓለምን ዞረው ያስተምራሉና:: ዞሮ፣ ተጉዞ፣ ተንገላቶ የሚያስተምር ሐዋርያ ይባላል:: እኛ ግን የምንመለከታቸው አስራ ሁለቱን ሐዋርያት ነው:: ይህንንም እንደሚከተለው እናያለን::

## ከመጠራታቸው በፊት

ቅዱሳን ሐዋርያት ወንጌልን እንዲሰብኩ ፣ድውያንን እንዲፈውሱ ፣ አጋንንትን እንዲያወጡ ከመጠራታቸው በፊት ጥቂቶቹ በተሻለ ኑሮ አብዛኞቹ ግን በዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ ነበሩ:: እነ ቅዱስ ታዴዎስ ፣ ቅዱስ ጴጥሮስ. . . ምንም የሌላቸው ደሀዎች ነበሩ:: በአንጻሩ ደግሞ በቀረጥ ሥራ ሀብታም የነበረ ቅዱስ ማቴዎስም ነበር:: በእውቀትም በኩል ስንመለከት ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስና ቅዱስ ያዕቆብ ምንም የማያውቁ ነበሩ:: ማቴ 20÷20 በሌላ መልኩ ደግሞ ትንቢተ ነብያት የሚያውቅ ምሁረኦሪት ቅዱስ ናትናኤልም ነበር:: « ቦኑ ይትከሃል እም ናዝሬት ይጻእ ኄር›› ብሎ የተናገረው መጻሕፍትን ስለሚያውቅ ነበር:: ዮሐ 1÷46 እናም ሐዋርያት በተለያየ ሥራ ይተዳደሩ የነበሩ ናቸው::

## በተጠሩ ጊዜ

አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ከአምስት የተለያየ ቦታ ጠርቷቸዋል::

- ከአናምያን /ሸመና/ :- በሸመና መረብ በመጥለፍ ቅዱስ ታዴዎስ፣ ልብዴዎስ የሚተዳደርበት ሥራ ነበር::
- ከኀነጽያን /ከግንበኝነት/ :- ቅዱስ ቶማስ ተጠርቷል::
- ከመጸብኀን /ከቀራጭነት/ :- ቅዱስ ማቴዎስ ተጠርቷል፡፤
- ከመሰግራን /አሣ አጥማጅነት/:- ቅዱስ ዮሐንስ ፣ጴጥሮስ ፣ ያዕቆብና እንድርያስ ተጠርተዋል::
- ከመስተገብራን/ከግብርና/:- እንደ ቅዱስ በርተሎሜዎስ ያሉ አባቶች ተጠርተዋል::

ከአምስት ቦታ የጠራቸው ቤት በአምስት ነገር እንዲሰራ (በጭቃ፣ በገለባ ፣ በሣር ፣ በድንጋይና በእንጨት) ነው። ከእናንተም አራቱን ባሕርያተ ሥጋ አምስተኛ ባሕርየ ነፍስን የተዋሐደ ሰውን እጠብቅባችኋለሁ ሲል ። እነርሱም ሁሉን ጥለው ተከትለውታል። ለጊዜው በእግር ኋላ ግን በግብር ።

ሲጠሩም ከፊት ከኋላ ምን አስቀድሟል ምን አስከትሏል ሳይሉ በእምነት ያላቸውን ጥለው ተከትለውታል። እርሱም የግማሾቹን ስም እየቀየረ ጠርቷቸዋል። ጌታቸው መሆኑን ለመግለጽ። አንድም ከብሉይ ያሳለፈው ያላሳለፈውም ሕግ እንዳለ ለማጠየቅ። ማቴ 9÷9፣ ሉቃ 6÷13፣ 9÷1፣ ማቴ 10÷1-5

## ለምን ተጠሩ?

1. *ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ*፡- ማን እንደሆነና የመምጣቱንም ዓላማ ተረድተው መልካም እንዲሰቱ ከእርሱ ጋር አኖራቸው። ዛሬም እኛ ለአገልግሎት ከመጠራታችን በፊት ከእግዚአብሔር ጋር በቤቱ ልንኖር ይገባናል። ለምን እንደጠራን? ምን እንደሚጠብቅብን ? ዓላማችን ምን መሆን እንዳለበት ? በአጠቃላይ ጽድቅንና ኃጢአትን የምንለየው ከእግዚአብሔር ጋር ስንኖር ነው። አምላካችን በጠራን ጊዜ ከእርሱ ጋር ለመኖር መሻት አለብን መዝ 72÷18 1ሳሙ 3 ÷1-10
2. ***እንዲሰብኩ /እንዲያስተምሩ /***፡- አመንኩ መሰከርኩ እንዲል ጌታችን የሚያዩትን የእጁን ተኣምራት የሚሰሙትን የቃሉን ትምህርት ሌሊት ምን ያደርግ እንደነበር በአጠቃላይ ስለ ክርስቶስ የባሕሪት አምላክነት ስለ ነገረ ድኅነት በማስተማር የሰዎችን ልቦና መልሰው መልካም እንዲሠሩ ዘረው እንዲያስተምሩ ዓለምን አሳምነው ደቀመዛሙርት ያደርጉ ዘንድ ነው። ማቴ 28 ÷19
3. ***ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ***፡- ሑሩ ወመሐሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም ተብለው የሚላኩ ናቸውና በዓለም ውስጥ ደግሞ ብዙ የሥጋና የነፍስ በሽተኞች እንዲሁም አጋንንት ያደረባቸው አሉና እነዚህን እንዲያድኑ ተጠሩ ። ሐዋ. 3÷10፣ 9÷40፣ 5÷17

## ለምን አሥራ ሁለቱን ብቻ መረጠ?

1. ***ትንቢቱን ለመፈጸም***፡- **ተረፈ ኤር. 11÷52 ‹‹. . . 12ቱ ሐዋርያትን ለእርሱ አገልጋዮች እንዲሆኑ ይመርጣል›› የሚል የተነገረ ትንቢት አለና። ምሳ 9÷1-6 በዚህ ጥቅስ ጥበብ የተባለች ቤተክርስቲያን ስትሆን አንድም ክርስቶስ ነው። ባሪያዎች የተባሉም ሐዋርያት ናቸው። ሐዋርያትንም ልካ ምእመናንን ትጠራለችና ነው።**

2. *ምሳሌውን እውን ለማድረግ፡-*

ሀ. የይስሐቅ ልጅ ያዕቆብ ሶርያ ወርዶ 12 ልጆችን ወልዷል። ጌታችንም ከሰማያት ወርዶ የአዳምን ባሕርይ ባሕርዩ አድርጎ 12ቱን ሐዋርያት መርጦ ሾሟል። ዕብ 2÷16

ለ. አባታችን ኢያሱ ሕዝበ እሥራኤልን የዮርዳኖስን ባሕር ሲያሻግራቸው 123 ካህናትን በዮርዳኖስ ባሕር እንዲቆሙ አዟል። ባሕሩም ደርቆ ከተሻገሩ በኋላ ድንጋዮን ተሸክመው ወደ ገሪዛን ተራራ ወስደዋል። 12 ካህናት መሆናቸው የሐዋርት ምሳሌ ሲሆን ድንጋዩ ደግሞ የመከራቸው ምሳሌ ነው።

ሐ. በኢያሱ መሪነት 12ቱ ነገደ እሥራኤል ምድረ ርስት እንደገቡ በ12ቱ ሐዋርያት ትምህርትም ያመኑ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉና።

## ሐዋርያት በክርስቶስ መዋዕለ ሥጋዌ

12ቱ ሐዋርያት በመዋዕለ ሥጋዌ ምንም የጐደለባቸው ያላዩት ነገር አልነበረም። ሁሉን ጥለው ተከትለውታልና ምሥጢሩን አሳይቷቸዋል። ማቴ 25÷ 26፣ ዮሐ 13÷1-28

- ከእግሩ ሥር ቁጭ ብለው ይማሩ ይጠይቁም ነበር።
- እየተላላኩ ያገለግሉ ነበር። ዮሐ 2÷10፣ 4÷ 1-42
- ከወገኖቻቸው ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ኅብረትም አልገቡም ነበር።

በአጠቃላይ ሐዋርያት ሁሉም ችለው ጸንተው ስለ ክርስቶስ አምላክነት መስክረዋል። ጌታችንም ሀብተ ክህነትን ሰጥቷቸዋል። ማንም ያልሰማውን አሰምቷቸዋል። በዚህም ተመስግነዋል። ሉቃ 10÷23፣ 18÷18 ፣ማቴ 16÷18፣ ዮሐ 6÷68

## የመጀመሪያው ተአምር

በሦስተኛው ቀን በገሊላ ቃና ሠርግ ሆነ። በዚያም ጌታችን ተገኝቶ የመጀመሪያውን ተአምር አደረገ። በሠርጉ ላይ እናቱ እመቤታችን 12ቱም ሐዋርያት ተገኝተዋል። በግብዣውም የወይን ጠጅ ባለቀባቸው ጊዜ በእመቤታችን አማላጅነት፣ ዘመዷ ዶኪማስን ልጇን ለምና ከውርደት ከሽሙጥ አድናዋለች። ዮሐ. 2÷1-11።

# ክርስቶስ ያስተማረው ትምህርት

## አንቀጸ ብፁዓን

የተራራው ስብከት በመባል የሚታወቀው እንደ ቤተክርስቲያናችን ስያሜ አንቀጸ ብፁዓን እየተባለ የሚጠራውን እንደ መጀመሪያ አዋጅ አድርጎ «ብፁዓን ብፁዓን» እያለ እውነተኛውን የክርስቲያንነት ትምህርት በዚህ መልክ አስተማረ:: ማቴ.5÷1-12:: ይህ ትምህርት የፍፁምነት ትምህርት ነው:: የክርስትናውም አርነት ፍፁም ነውና አንድ የመንግሥት መሪ መንግሥት እንደያዘው የሚያውጀው የመንግሥቱን ዓላማ ነው:: ክርስቶስ በመጀመሪያው የክርስትናውን ዓላማ ይህንንና ይህን ሠርቶ የፈፀመ ብፁዕ ነው በማለት እውነተኛውን ክርስቲያናዊ ትምህርት አስተማረ::

ምንም በተለያዩ ቦታዎች ብፁዓን ቢጠሩም በዚህ በተራራው ትምህርት ጊዜ የተገለጡት እንደ ቅዱስ ማቴዎስ አገላለጥ ዘጠኝ ናቸው::

## ትምህርቱ በምሳሌ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር እንዲሁ ቢገባው ይግባው ካልገባውም ይቅር በማለት አልነበረም:: ነገር ግን ሁሉንም በሚገባው በምሳሌ ያስተምር ነበር:: ለምሳሌ ገበሬዎችን በእርሻ፣ በዘር እየመሰለ አስተምሯል:: ማቴ.13÷3-50፣ ማር.4÷13-20፣ ሉቃስ 8÷4-15:: ለሴቶች በዱቄት፣ በእርሾ እየመሰለ አስተምሯል:: ማቴ.13÷33:: ለነጋዴዎች በመክሊት በልዩ ልዩ ሚዛን እየመሰለ አስተምሯል:: መንግሥተ ሰማያትን በልዩ ልዩ ምሳሌዎች እየመሰለ አስተምሯል:: እንዲያውም ያለምሳሌ ኣላስተማረምም አልተናገረምም:: ማቴ.13÷35:: እንግዲህ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዓላማ ለማስተማር ስለሆነ ሁሉንም በሚገባው መልክ አስተ ምሯል::

## የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራት

ድውያነ ነፍስን በትምህርት እየፈወሰ፣ ድውያነ ሥጋን በተአምራት ይፈውስ ነበር:: ከተአምራቱም በጥቂቱ ሕብስት አበርክቶ ማብላቱ ማቴ.15÷32-38፣ ህሙማንን መፈወስ ዮሐ. 5÷5-10፣ ዕውራንን መፈወስ ዮሐ.9፣ ሙት ማንሳት ዮሐ.1÷11-34 ..በአጠቃላይ ብዙ ገቢረ ተአምራትን ፈጽሟል:: ግን ድውይ በመፈወሱ ተአምራትን ሁሉ በማድረጉ ሰንበትን ሻረ ተብሎ ተከሷል:: ሰይጣንን በሰይጣን አለቃ ያወጣል ተብሎ ተከሷል::

## ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማኅበራዊ ኑሮ

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነው ሰውን መስሎ ሰው በሄደበት ሄዶ ለማስተማር ነው:: በሰዎች ማኅበራዊ ነገሮችም እየገባ የደስታቸውም የኃዘናቸውም ተካፋይ ሆኗል:: በመጀመሪያ ጊዜ በገሊላ ቃና ተአምራትን ያደረገው በሠርግ ቤት በመገኘት የሰዎች የደስታ ተካፋይ ከመሆኑ የተነሣ ነው:: ዮሐ. 2÷1-12::

ከቅዱስ ማቴዎስ ቤት ጀምሮ በነአልዓዛር፣ ስምዖን ዘለምጽ ቤት ግብዣ እየተጋበዘ ገብቷል:: በእነዚህም ቤቶች ቀዳሚ የሆኑ ትምህርቶችን ሰጥቷል:: ሉቃስ 10÷38-42:: በቤተ መቅደስ ተገኝቶ የጸሎቱ ተካፋይ ለመሆን ከ12 ዓመት ዕድሜው ጀምሮ ፈጽሟል:: ሉቃስ 2÷42-50:: እኔ አምላክ ነኝና እኔ ያለሁበት ነው ቤተመቅደስ አላለም:: ይህም ሰው እምነቱን ሥርዓቱ አክብሮ በማኅበር ጸሎት በተወሰነው ቦታ መገኘት ግዴታው መሆኑን ያስረዳል:: በሐዘን ቤት ተገኝቶ ተንሰቅስቆ አልቅሷል:: ይኸውም በአልዓዛር ሞት ጊዜ ነው:: በዚያም ከመገኘቱ የተነሣ አልዓዛርን ከሞት አስነስቶታል:: ዮሐ.11÷11-34:: በዚህም መልክ እንደማንኛውም ሰው ሆኖ ከኃጢአት በቀር የሰውን ችግር እየተካፈለ፣ እግረ መንግዱን ግን እያስተማረ ኖረ:: ሲያስተምር ውሎ የሚያድርበት ቤት የሚያርፍበት ክፍል አልነበረውም:: ቀን በምኩራብ በአዳራሽ ሁሉ ሲያስተምር ይውላል:: ሌሊት ግን ወደ ደብረ ዘይት እየወጣ ያድር ነበር:: ሉቃስ 21÷37:: ምግብ የሚያዘጋጅለት፣ ደከመህ እረፍ የሚለው ዘመድ አልነበረውም:: ሲያስተ ምር ውሎ «ልጆች የሚበላ አለን?» እያለ ይጠይቅ ነበር:: ማቴ. 15÷32-38:: ማቴ. 21÷1-17፣ ሉቃስ 19÷29-48::

### የሐሙስ እራት

ጌታችን ከደቀመዛሙርቱ ጋር የፍስሐን /የፋሲካን/ በዓል በአልዓዛር ቤት በሚያከብርበት ሰዓትኅብስቱን አንስቶ ባረከ፣ ፈተተ፤ ለደቀ መዛመርቱም «እንኩ፣ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው ነገ በመልዕልተ መስቀል የሚቆረሰው» ብሎ ሰጣቸው:: ጽዋውንም አንስቶ እንዲሁ ባረከ «እንኩ ሁላችሁ ጠጡ ይህ ነው የሀዲስ ኪዳን ደሜ ለዓለም ኃጢአት ማስተስርያ ሆኖ ነገ የሚፈሰው» ሲል ሰጣቸው:: ማቴ. 26÷26-29:: በዚህ ጊዜ ሥርዓተ ቁርባንን አሳያቸው:: ምስጢረ ቁርባንን መሠረተላቸው:: ከዚያም ጊዜ ጀምሮ በክርስቶስ የሚያምን ሁሉ ከእርሱ ጋር ግንኙነት ሳያቋርጥ 1ኛ ቆሮ.11÷26 ይኖር ዘንድ ሥጋውን መብላት ደሙን መጠጣት አስፈላጊ መሆኑን አስረዳ:: ከዚህ በኋላ ደቀመዛሙርቱን ይዞ ለጸሎት ወደ ጌቴ ሰማኔ ሄደ:: ማቴ.26÷36-49::

## የጌታችን መያዝ

ጌታችን በጌቴሴማኒ ሆኖ ሲጸልይ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ የነበረ ይሁዳ ወደ ካህናቱ አለቃ ሄዶ ነገር ሠራ:: ያስይዘውም ዘንድ ሠላሳ ብር ተቀብሎ የጭፍሮቹ መሪ ሆኖ ድንገት እርሱ ክርስቶስ ነውና ተባብራችሁ ያዙት ብሎ ምልክት ሰጥቷቸው ነበርና ይሁዳ ሄዶ «መምህር ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን» ሲል እጅ ነሳው:: በዚህ ጊዜ ተረባርበው ያዙት:: ክርስቶስ ግን «ይሁዳ በመሳም ልታሲዘኝ መጣህን» ሲል የሰላም ቃል ተናግሮ እጁን ሰጠ እንጂ «አልያዝም» ብሎ አልታገለም:: ወዲያውም ጭፍሮቹ እያዳፉ እያጋፉ ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ወሰዱት:: ማቴ. 26÷47-57::

ደቀመዛሙርቱ ግን ለራሳቸው ፈርተው ተበተኑ:: ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ብቻ የሚሆነውን ሁኔታ ሁሉ ለማየት ከኋላ ከኋላ እየተከተሉ እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ አብረው ሄዱ:: ቅዱስ ዮሐንስ ግን እስከ መጨረሻውም ቢሆን አልተለየውም:: ስለዚህ በመስቀሉም ጊዜ በአንጻሩ ሆኖ ሲያለቅስ ውሏል:: ማቴ. 26÷58፣ ዮሐ. 19÷26:: ሊቀ ካህናቱም አጣድፎ የበኩሉን ምርመራ ፈጸመና በክርስቶስ ላይ ሊሞት የሚያስችለውን ውሳኔ በበኩሉ አስወስኖ ወደ ጲላጦስ ወሰደው:: ጲላጦስ ግን ነገሩን መላልሶ በማጥናት ምንም በደል ያልተገኘበት መሆኑን ተረድቶ ሊለቀው ፈልጎ ነበር::

ነገር ግን የካህናቱ አለቃ፣ የሕዝብ ሽማግሌዎችም በአንድ ድምጽ ሆነው «ስቀለው አስወግደው» እያሉ ጮሁ:: በመቀጠልም «ይህን ሰው ከአዳንከው የቄሣር ታማኝ አይደለህም ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ነው:: ይህ ሰው የቄሣር ጠላት ነው:: ለቄሣር ሰዎች ግብር እንዳይከፍሉ ከልክሏል» ሲሉ ከቄሣር ጋር እንደሚያጣሉት አስፈራሩት:: በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ሕጋችን ሞት ይገባዋል ብለው የነበረውን ሕግ ስለጠቀሱበት እንደ ሕጋችሁ ወስዳችሁ ስቀሉት ብሎ ክርስቶስን አሳልፎ ሰጣቸው:: ጲላጦስ ግን ከነገሩ ንፁህ እንደሆነ ተናገረ:: ማቴ. 27÷15-26፣ ለቃስ 23÷1-25፣ ዮሐ. 18÷28

## ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ክፉ አድራጊ ተሰቀለ:: በመስቀል ተሰቅሎ የሞተ ሁሉ እርጉም ይባል ነበርና እርግማንን ውርደትን ከሰው ለማራቅ ሲል በእንጨት ተሰቀለ:: ወንጀሉንም ከፍተኛ ለማድረግ በነፍስ ገዳይና በልዩ ልዩ ወንጀል ከተፈረደባቸው ሁለት ወንበዴዎች ጋር ተሰቀለ::

ክርስቶስ በሰው ዘንድ እንደ ክፉ አድራጊ ቢቆጠርም ሌላው ግዑዝ ፍጥረት ሁሉ ለአምላክ ለመመስከር ወደ ኋላ አላለም:: ስለዚህ ፀሐይ፣ ጨለማ፣ ጨረቃ፣ ደም ሆኑ፤ ከዋክብት ረገፉ፣ አእባን ተፈተቱ፣ መቃብራት ተከፈቱ፣ ሙታን ተነሱ፣ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተቀደደ:: ማቴ.27÷45-54፣ ማር. 15÷33፣ ሉቃስ 23÷44-45::

ካህናቱ ፍላጎታቸው የክርስቶስን ሕይወት ለማጥፋት ነበር:: ይኸውም ፈቃዳቸው ተፈጸመ፣ የክርስቶስ ፈቃድ ደግሞ ስለሰው ሕይወት ተላልፎ መሞት ነበር:: እርሱም ተፈጸመ:: እንዲሁም በሰው በኩል የሚቻለው የክፋት ሥራ ሁሉ እስከ ሞት ድረስ ነበር:: በእርሱ ሁሉ ተፈጸመ:: ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ ሁሉም ተፈጸመ ሲል የመጨረሻውን ቃል ተናግሮ ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው በሥልጣኑ ለየ:: ዮሐ. 19÷30:: የክርስቶስ ሞትም በእናቱ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያምና በቅዱሳን ደቀመዛሙርቱ በኩል መራራ ሐዘን ሆነ:: በጸሐፍትና በሊቀ ካህናቱ በኩል ደግሞ ታላቅ ደስታ ሆነ::

## *የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መቀበር*

ንጉሥ የሰቀለው፣ አንበሳ የሰበረው ይፈራልና በመስቀል ተሰቅሎ የሞተውን ኢየሱስን ለመቅበር የተረፉት አበጋዞች ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የተባሉ ሽማግሌዎች ጥያቄ አቀረቡ:: ጲላጦስም እንደሞተ በሰማ ጊዜ ተደነቀ:: በመስቀል ሳለ የተደረገውን ተአምራት ሰምቶ ስለነበር በእውነት ይህ ሰው ታላቅ ነው ብሎ በመስቀሉ ተጸጽቶ ነበርና ዮሴፍና ኒቆዲሞስን በጠየቁት መሠረት እንዲቀብሩት ተፈቀደላቸውና በአዲስ በፍታ ገንዘው ማንም ወዳልተቀበረበት ቦታ ወስደው ዮሴፍ ለራሱ ባዘጋጀው በአዲስ መቃብር ውስጥ ቀበሩት:: ማቴ.27÷56-61፣ ማር.15÷42፣ ሉቃስ 23÷50-56፣ ዮሐ.19÷38-42:: ከአብና ከመንፈስ ቅዱስም ጋር በክብሩ አልተለየምና ዓለምን ይገዛ ያስተዳድር ነበር:: መቃብር ጠባቂዎቹ ተመድበው /ማቴ. 25÷62-66/ በመቃብሩም ቁልፍ ተደርጎለት በማኅተም ታተመ:: ክርስቶስ ግን መቃብሩን ከፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል በሦስተኛው ቀን በሥልጣኑ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ:: ማቴ.28÷7፣ ማር.16÷6፣ ሉቃስ 24÷5፣ ዮሐ.20÷16

## የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ

ክርስቶስ በተቀበረ በሦስተኛው ዕለት በመንፈቀ ሌሊት ሲነሣ የመቃብር ጠባቂዎች ደነገጡ በድንም ሆኑ:: ክርስቶስን ከልደት እስከ መስቀል ሞት ድረስ በደካማነት መልክ እንደሰው ብቻ ይመለከቱት ነበር:: ነገር ግን በትንሣኤው እፁብነት /ድንቅ መሆን/ አምላክነቱን አሸናፊነቱን አሳመነ:: ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውምና ይዞም ሊያስቀረው አልቻ ለም:: ማቴ. 28÷4::1.ቆሮ.15÷56 በክርስቶስ ሞት ያዘኑት ሐዋርያት ቅዱሳት አንስትም ፀጥታ ሳያገኙ ሰንብተው ነበር:: በዚህ ቀን ግን በየበኩላቸው ወደ መቃብር እየሄዱ ከመቃብር አካሉን ስላጡ በበለጠ አዘኑ:: ሴቶች ደግሞ ከመመላለሳቸው የተነሳ መልአኩ «እንዴት ሕያውን ከሙታን ጋር ትፈልጉታላችሁ? እርሱ ተነስቷል ከዚህ የለም» የሚል የሚያስደስትም የሚያሳዝንም ቃል ሰምተው ተመለሱ:: እያዘኑም ሲሄዱ ክርስቶስን በመንገድ አገኙት፤ እጅም ነሱት /ሰገዱለት/:: ማቴ.28÷5-10:: እርሱ ግን «ሂዱና ለደቀመዛሙርቱ እንደተነሣሁ ንገሯቸው» አላቸው:: በክርስቶስ መነሣት በደቀመዛመርቱ በኩል ፍፁም ደስታ ሲሆን፣ በሊቃነ ካህናቱ በጸሐፍቱ በኩል ደግሞ ሀዘንና ፍርሃት ሆነ:: ስለዚህም ትንሣኤው ለሕዝብ እንዳይነገር እኛ ተኝተን ሳለ ደቀ መዛመርቱ መጥተው ወሰዱት ተ ብሎ እንዲነገር አስደረጉ:: ማቴ. 28÷9:: እንዲሁም ከእነርሱ ጋር እየወጣና እየወረደ እንደቀድሞው እየበላና እየጠጣ አርባ ቀን አብሯቸው ቆየ:: የሐዋ.ሥራ 1÷1-4::

## የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት

ጌታችን ከተነሣ በኋላ በዚህ ዓለም የሚፈጽመው ሌላ ተልዕኮ ስለሌለው የቆየው አርባ ቀን ብቻ ነው:: ከዚህ በኋላ ወደ ላከው ወደ አብ ዐረገ:: የሐዋ. ሥራ 1÷1-4:: ደቀመዛሙርቱ ተሰብስበው ባሉበት የማጽናኛ ቃል እንዲህ ብሎ ተናገረ እናንተ ግን ኃይል እስክትለብሱ ድ ረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ ብሎ ተናግሮ ዐረገ:: ሉቃስ 24÷48-52::

ደቀ መዛመርቱም እጅ ነስተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ:: ሉቃስ 24÷50-52:: 120 የሚያህሉ ቤተሰቦች ሳይለያዩ የተስፋውን ቃል ይጠባበቁ ነበር:: የሐዋ. ሥራ 1÷15:: 120 ቤተሰብ የሚባሉት 12ቱ ሐዋርያት፣ 72ቱ አርድዕት፣ 36ቱ ቅዱሳት አንስት ነበሩ:: ቅድስት ድንግል ማርያምም ከእነዚህ ሁሉ አልተለየችም ነበር::

## ጽርሐጽዮን

- ይህ ቅዱስ ሥፍራ የማርቆስ እናት የማርያም ቤት ነው።
- የዚህ ቤት አገልገሎት ከዕርገት በኋላ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ ሉቃ 24÷49 በተባሉት አምላካዊ ቃል መሠረት ጌታ ባረገ በአሥረኛው ቀን በኢየሩሣሌም ባለችው የማርያም ቤት በጽዮን አዳራሽ በታቦት የምትመሰል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከመሀል አድርገው በጸሎት ሲተጉ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ ተቀምጠውበትም የነበረውን ቤት ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ሞላው እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በእያንዳንዱ ያደረ መንፈስ ቅዱስ ምሥጢርን አናገራቸው። ሉቃ 22÷7-23 ። ሐዋ 2÷1-42 የመጀመሪያው የሐዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ጽርሐጽዮን ናት። በጽርሐጽዮን የሞላ የመንፈስ ቅዱስ ሀብት ዛሬም ቤተክርስቲያንን አይለያትም። ሐዋርያት የትምሕደው ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ሊሰክሩ የቻሉት እመቤታችንን ከመሀል አድርገው በጽዮን አዳራሽ በተቀመጡበት ጊዜ ነው ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሌለችበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስ አይወርድምና። መንፈስ ቅዱስን የሚሻ እመቤታችንን መጠጊያ አድርጎ በጽዮን አዳራሽ /ቤተክርስቲያን/ ጸንቶ መቀመጥ አለበት። ቤተክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ግምጃ ቤትና የምሥጢር መፍለቂያ ምንጭ ናትና።

## ጽርሐጽዮን

- ይህ ቅዱስ ሥፍራ የማርቆስ እናት የማርያም ቤት ነው።
- የዚህ ቤት አገልገሎት ከዕርገት በኋላ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ ሉቃ 24፥49 በተባሉት አምላካዊ ቃል መሠረት ጌታ ባረገ በአሥረኛው ቀን በኢየሩሣሌም ባለችው የማርያም ቤት በጽዮን አዳራሽ በታቦት የምትመሰል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከመሀል አድርገው በጸሎት ሲተጉ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ንፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ ተቀምጠውበትም የነበረውን ቤት ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ሞላው እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በእያንዳንዱ ያደረ መንፈስ ቅዱስ ምሥጢርን አናገራቸው። ሉቃ 22፥7-23 ። ሐዋ 2፥1-42 የመጀመሪያው የሐዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ጽርሐጽዮን ናት። በጽርሐጽዮን የሞላ የመንፈስ ቅዱስ ሀብት ዛሬም ቤተክርስቲያንን አይለያትም። ሐዋርያት የተምሔደው ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ሊሰክሩ የቻሉት እመቤታችንን ከመሀል አድርገው በጽዮን አዳራሽ በተቀመጡበት ጊዜ ነው ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሌለችበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስ አይወርድምና። መንፈስ ቅዱስን የሚሻ እመቤታችንን መጠጊያ አድርጎ በጽዮን አዳራሽ /ቤተክርስቲያን/ ጸንቶ መቀመጥ አለበት። ቤተክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ግምጃ ቤትና የምሥጢር መፍለቂያ ምንጭ ናትና።

## ዋቤመጻሕፍት


1. መጽሐፍ ቅዱስ
2. የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ /አባ ጎርጎርዮስ/
3. መጽሐፈ ክርስትና ቁ.2 - አባ መልከጼዴቅ
4. ሐመር 9ኛ ዓመት ቁ.3
5. ነቅዓ ገነት - ዲ/ን ኃይለጊዮርጊስ ተፈራ
6. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቁ.192 - ዲ/ን አባይነህ ካሴ
7. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት
8. ኆኅተ ሰማይ - ዲ/ያ ያሬድ ገ/መድህን
9. የቤተክርስቲያን ታሪክ - በሉሌ መልአኩ
10. ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት - ማኅበረ ቅዱሳን
11. ሁለቱ ኪዳናት - ማኅበረ ቅዱሳን
12. ውዳሴ ና ቅዳሴ ማርያም አንድምታ
13. መጽሐፈ ቅዳሴ አንድምታ
14. ኦሪት ዘፍጥረት አንድምታ
15. ኦሪት ዘጸአት አንድምታ
16. ሠለስቱ ሀዲሳት አንድምታ
17. መዝገበ ታሪክ ቁ. 1 ና 2 - ሊቀኅሩያን ኤርሚያስ
18. ደስታ ተክለ ወልድ መዝገበ ቃላት


**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**
**በመናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት ትምህርት ክፍል የተዘጋጀ።**


ዌብ ሳይት http/www.stgeoressc.net

ኢሜይል፡georgesaint42gmail.com


**፳፻፲፩ ዓ.ም.**